የወ/መ/ቁጥር 160603

የልደታ ምድብ 1 ኛ ወንጀል ችሎት

ሰኔ 17 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፡ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፡ ወ/ሮ ዴሴ ዳዲ ዋቃየ - ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

ፍርድ

ዐ/ሕግ ህዳር 07 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የወንጀል ክስ አቤቱታ በአንደኛው ክስ ተከሳሽ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 615 ላይ የተደነገገውን በተመላለፍ የሰውን ክብር ለመንካት በማሰብ ጥቅምት 07 ቀን 2002 ዓ.ም ከቀኑ 9፡00 ሰዓት ሲሆን በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 ልዩ ቦታው ወይራ ሰፈር አካባቢ የግል ተበዳይ ወ/ሮ ኩሪ ዳዲን ቡትዶ ለቃቃሚ በማለት ቀጥታ የተናገራቻት በመሆኑ በፈፀመችው የስድብና ማወረድ ወንጀል ተከሳለች ሲል፤ በሁለተኛው ክስ ደግሞ ተከሳሽ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 580 ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ በው ላይ ድንጋጤን በሚቀሰቅስ ሁኔቴ ጉዳት የምታደርስ መሆኗን በመግለፅ በአንደኛው ክስ ላይ በተጠቀሰው ቀን፤ ሰዓትና ቦታ የግ ተበዳይ ወ/ሮ ኩሩ ዳዲን ድጅኖ ብረት አንስታ ለመማታት ስታስፈራራት የአካባቢ ሰዎች ያስቀሯት በመሆኑ በፈፀመችው የዛቻ ወንጀል ተከሳለች በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሽ ደርሷትና ተነቦላት ከተረዳችው በኋላ ክሱን ሳትቃወም፤ ድርጊቱን፤ አልፈፀምኩም፤ ጥፋተኛም አይደለሁም ብላ ክዳ በመከራከሯ ዐ/ሕግ የግል ተበዳይን ጨምሮ ሁለት ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን ምስክሮቹም እንደ ዐ/ሕግ የክስ አቀራረብ ያሰረዱ ስለሆነ ተከሳሽ በሁለቱም ድንጋጌዎች ስር እንድትከላከል በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(1) መሰረት ታዛላች።

ተከሳሽም እከላከላለሁ ብላ አንድ የመከላከያ ምስክር አቅርባ ያሰማች ሲሆን በመከላከያ ጭብጥነትም በወቅቱ የግል ተበዳይ እኔን አባራ ወደቤቴ ጉብቼ ሰዎች መጥተው ገላገሉኝ እንጅ የተናገርኩት ነገር የለም በማለት አስመዝግባ በዚሁ መሰረት ምስክሯ ቀርባ የመሰከረች ሲሆን ቃሏም ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ይገኛል።

ፍ/ቤቱም ተከሳሽ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበባትን ክስና ማስረጃ አስተባብላለች ወይ የሚለውን ነጥብ የመረመረ ሲሆን የተከሳሽ አንድ የመከላከያ ምስክር በወቅቱ በቦታው ነበርኩ የግል ተበዳይ

የተከሳሽን መቆፈሪያ ይዛ ስትሮጥ ነበር፤ ከዚያ ሁለቱ ተያያዙና ጩኸት ሲሰማ ሰዎች መጡ በማለት ያስረዳች ቢሆንም በወቅቱ የግል ተበዳይና ተከሳሽ የተያያዙ ከሆን በክሱ ላይ የተመለከተውን ነገር ተከሳሽ አልፈፀመችም የሚያስብል ነገር አይደለም። ምክንያቱም ሁለቱ በወቅቱ ከተያያዙ መነጋገራቸው የማይቀር ሲሆን፤ ከተነጋገሩ ደግሞ ይህን በክሱ ላይ ተከሳሽ ፈፀመች የተባለውን ድርጊት አልፈፀመችም የሚያስብል ባለመሆኑ ተከሳሽ ባቀረበችው የመከላከያ ማስረጃ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበባትን ክስና ማስረጃ ያላስተባበለች ስለሆነ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 615 እና 580 ስር ጥፋተኛ ናት በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ውሳኔ ተሰጥቷል።

የቅጣት አስተያየት

ዐ/ሕግ፡ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 85 መሰረት ጥፋቱ ተደራራቢ ስለሆነ፤ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84(1)(ሠ) መሰረት ደግሞ ተከሳሽ ድርጊቱን በእህታቸው ላይ ስለፈፀሙ ከብዶ እንዲወሰን በማለት አመለከተ።

ተከሳሽ፡ ዕድሜዬ 60 ዓመት ነው፤ ትዳር አሁን የለኝም፤ ነገር ግን አራት ልጆችንና ሌሎች የዘመድ ልጆችን እየረዳሁ አስተዳድራለሁ፤ የጡረታ ገቢ ብር 400.00(አራት መቶ ብር) ፤ ቤት በማከራየት ደግሞ በወር ብር 500.00(አምስት መቶ ብር) አካባቢ አገኛለሁ በማለት አመለከቱ።

ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ቅጣት ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ሊሆን እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወስነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ክብደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

ተከሳሹ አሁን ጥፋተኛ የተባለበት በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 580/የዛቻ ወንጀል እና አንቀፅ 615/የስድብና ማዋረድ ወንጀል ገና ደረጃ ያልወጣላቸው በመሆኑ የወንጀል ደረጃ እና እርከን የሚወሰነው በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 13 መሰረት ነው። የደረጃ አወሳሰኑም ማክበጃውና ማቅለያው ታሳቢ ከመደረጉ በፊት በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት እንደሚወሰን መመሪያው በደነገገው መሰረት ደረጃው በሦስት ደረጃዎች ሀ. ዝቅተኛ፤ ለ. መካከለኛ እና ሐ. ከባድ ደረጃ በማለት ይለያል።

ፍ/ቤቱም በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት የወንጀሉን ደረጃ ለመወሰን ሲል አፈፃፀሙን ሲመለከተው የተፈፀመው በዕለት ግጭትና ከውርስ ንብረት ጋር በተያያዘ በመሆኑ፤ የግል ተበዳይም የራሳቸው የተወሰነ ድርሻ የነበራቸው መሆኑንና ዐ/ሕግም የወንጀል ደረጃው ዝቅተና ተብሎ ቢወሰን ያለውን መሰረት በማድረግ የስድብና ማዋረድ ወንጀሉን በተመለከተ ደረጃው ዝቅተና ተብሎ የዛቻ ወንጀሉ ግን የተፈፀመው ተከሳሽ በወቅቱ የብረት ድጂኖ በመያዝ ስለሆነና በወቅቱ ገላጋይ ደርሶ ከጉዳቱ ያተረፋቸው ስለሆነ ደረጃው ከባድ ተብሎ ተወስኗል።

በወጣው ደረጃ መሰረት እርከን ለመወሰን በሕጉ አንቀፅ 580 ለወንጀሉ የተቀመጠው ቅጣት ከአምስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከስድስት ወር እስራት፤ ለወንጀል ሕግ አንቀፅ 615 ላይ ለተመለከተው ደግሞ ከሦስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከሦስት ወር በማይበልጥ እስራት ያስቀጣል። ከሁለቱ የቅጣት አይነቶች በቅድሚያ ፍ/ቤቱ አንዱን መለየት ስላለበት ተከሳሽና የግል ተበዳይ እህትማማቾች ቢሆኑም ከተፈፀመው የወንጀል ድርጊት አንፃር ተከሳሽን ያርማል፤ ወደፊትም ያስተምራል ብሎ ፍ/ቤቱ ባመነበት በእስራት እንዲቀጡ ተወስኗል።

ከዚህ በላይ በተመለከተው የቅጣት ደረጃ መሰረት እርከኑን ለመወሰን እያንዳንዱ የወንጀል ድንጋጌን ለአራት እኩል በማካፈል የሚመጣው ስሌት ለዛቻ ወንጀሉ ከዘጠና አምስት ቀን እስከ አንድ መቶ ሰላሳ ሰባት ቀን ተኩል ቀላል እስራት ሲሆን ለስድብና ማዋረድ ወንጀሉ ከአስር ቀን እስከ ሰላሳ ቀን ቀላል እስራት ነው። በዚህ መሰረት ለስድብና ማዋረድ ወንጀሉ መነሻ ቅጣቱ ሰላሳ ቀን ሲሆን ለዛቻ ወንጀሉ ደግሞ አንድ መቶ ሃያ ቀን ነው። ተከሳሽ ተደራራቢ ጥፋት ስለፈፀሙ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 184(1) (ለ) መሰረት የሁለቱ ቅጣት ድምር አንድ መቶ ሃምሳ ቀን ማለትም አምስት ወር ሲሆን ይህ ደግሞ በአባሪ አንድ መሰረት በእርከን 4 ላይ የተመለከተ ስለሆነ የእርከን 4 ደግሞ ፍቅድ ስልጣኑ ከአራት ወር እስከ ሰባት ወር ነው።

ከዚህ በመነሳት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት አመዛዝኖ ለመወሰን ዐ/ሕግ በተጠየቀው መሰረት በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 84(1)(ሠ) መሰረት ተከሳሽ ድርጊቱን የፈፀመችው በእህቷ ላይ ስለሆነ ቅጣቱ ከብዶ እንዲወሰን በማለት ያመለከተ ሲሆን፤ በዚህ መሰረት እርከኑ ወደ 5 ከፍ ብሏል።

ተከሳሽም የቅጣት አስተያየት እንዲያቀርብ ተጠይቀው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82 እና 86 መሰረት በማስረጃ የተደገፈ ያላቀረቡ በመሆኑ የቅጣቱን እርከን ዝቅ አላደረውም።

ስለሆነም ከላይ እንደተገለፀው ቅጣቱ በአባሪ አንድ እርከን 5 ላይ የተመለከተው ፍቅድ ስልጣን/range/ ከስድስት ወር እስከ ዘጠኝ ወር እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን በስድስት ወር ቀላል እስራት እንድትቀጣ ተወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. ተከሳሽ በአሁኑ ወቅት የልጆች አስተዳዳሪና ረዳት መሆናቸውንና ዕድሜአቸው 60 ዓመት መሆናቸውን ከግንዛቤ በማስገባት ለተከሳሽ አንድ ዕኑ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው የወደፊት አመላቸውና ፀባያቸውን ማየቱ በቂ ስለሆነ የእስራት ቅጣቱን በወንጀል ሕግ አንቀፅ 192 መሰረት በሁለት ዓመት ገደብ ታግዷል።

2 ኛ. ተከሳሽ እስከ ሁለት ዓመት ጊዜ ድረስ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 197(2) መሰረት ለመተማመኛ ዋስትና እንዲሆን ለብር 500.00(አምስት መቶ ብር) የሚበቃ ዋስትና ይጥሩ ወይም ተመጣጣኝ ዋስትና ይጥሩ።

3 ኛ. ተከሳሽ ለመንግስት የፅህፈት ወጪ ብር 25.00(ሃያ አምስት ብር) ይክፈሉ።

4 ኛ. ተከሳሽ የዋስትና ግዴታውን ሲጠሩና የፅህፈት ወጪውን ሲከፍሉ ይለቀቁ።

5 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

6 ኛ. በዚህ መዝገብ የተገባ የዋስትና ግዴታ ቀሪ ሆኗል።

7 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።